# መመሪያ ቁጥር 25/2001

## ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

በቆዳና ቆዳ ውጤቶች ዘርፍ የተሠማሩ ኢንዱስትሪዎች ለውጭ ገበያ የሚያቀርቡት ምርት ደረጃ ተሻሽሎ አገሪቱ ከዘርፉ የምታገኘው የውጭ ምንዛሪ ከፍ እንዲል ለማድረግ ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳ ላይ ታክስ የተጣለ በመሆኑ፣

ይሁን እንጂ የታክሱ መጣኔ አነስተኛ በመሆኑ ምክንያት በበቂ መጠን ተጨማሪ እሴት ያልታከለባቸው በከፊል የተዘጋጁ የቆዳ ውጤቶች ለውጭ ገበያ መቅረባቸው ካለመቋረጡም በላይ ከጊዜ ወደጊዜ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳ ብዛት እየጨመረ በመሄዱ፣

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል የወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 አንቀጽ 7(1) የታክሱን መጣኔ የማሻሻል ሥልጣን ለገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር የሰጠ በመሆኑ፣

ከዚህ የሚከተለው መመሪያ ወጥቷል።

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ «ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 25/2001» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## 2. <u>ማሻሻያ</u>

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳ ላይ የሚከፈለው ታክስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

1. ዌት ብሉ የበሬ ቆዳ ከዋጋው 150%
2. ፒክል የበግ ሌጦ ከዋጋው 150%
3. ዌት ብሉ የበግ ሌጦ ከዋጋው 150%
4. ዌት ብሉ የፍየል ሌጦ ቆዳ ከዋጋው 150%

## 3. <u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ መመሪያ ከጥር 1 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*ሱፍያን አህመድ*
*የገንዘብና የኢኮኖሚ ልማት*
*ሚኒስትር*